# የፖለቲካ ገለባና ገፈራ

# በሲያትል

ከአስተዋይ በቀለ

ሲያትል፣ መቀደዱ የባሰ እንደሚሆን አልገባት ብሎ ባረጀ ልብስ ላይ አዲስ እራፊ እለጥፋለሁ ብላ ያገር ፍቅራቸው ያደፈ፣ልባቸው ከጠባብ ብሔረተኝነት ያልጸዳ፣ ከኢትዮጵያዊነት የራቁ፣ በሽኩቻ ታፋቸው የሰለለ፣ ሀሳብ ያለቀባቸውና ፖለቲካቸው መንገድ ላይ ሊቆም የተቃረበ፣መቅሰፍትና እርግማን የበቀለባቸውን ድርጅቶችን ጋብዛ፣ ሰባ-ሰግል ነን ባዮች በተገኙበት በከንቱ ስትባክንና ራሷን ስታውክ ከርማ ፍሬዋ ገለባና ገፈራ ሆኖ ቀርቷል።

ድሮስ ! የኢትዮጵያ ፎረም ጊጉያን ሆኖ ነው እንጂ የሚወዷትን ሕይወታቸውን በጂንቶኒክና በቮድካ እቶን አቃጥለው የጨረሱ ሰባ-ገደል የፖለቲካ መሸተኞች ጋር የት ሊደረስ?

ያን ከንቱ አሚና እንቶወው፣ ምክንያቱም ባዶ ቀለህ ይዞ የሕልም ውሃ እየጠጣና ከድርጅተ-አጋንት ጋር ማርጌ-ቻቻ እያለ የኢትዮጵያ አምላክ ተቆጥቶ መንገዱን ዘግቶበታል።

የነፃ ጊልደር ቁንጣን አላሳርፈው ብሎ የሚዝለጠለጠው ምዝልዝል ደግሞ፣ ቢካን ኖሮ ጥሩ ዘኬ ለቃሚ መናፍቃን ቄስ በወጣው ነበር። ፖለቲከኛስ አይደለም። በወያኔ መሪነት የተቀመጠባትን ያችን ትንሽ የበረሃ ድንጋይ ኩርሲ ከሴራና ከፍንቀላ ማዳን አቅቶት በሴረኛ ጠላቶቹ ዶንያ ውስጥ ተከትቶ ጠረፍ ላይ የተወረወረና ሳይፍጨረጨር በዚያው ሰሎ የቀረ ሰው ሲሆን፤ እሾህን በእሾህ ስልት የተቃውሞ ሚና ይጫወታል ብሎ ማመን የፖለቲካ ቦቃነት ነው። ምንም ቅድመ ሁኔታ የለንም ብሎ ለፀረ- ኢትዮጵያ ከንቱ ኃይሎች ያቀረበውን የእጂ መንሻ ደግሞ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰምቶ በመታዘብ በሱና በድርጅቱ ላይ በሩንና መንገዱን ዘግቶበታል።

ሌላው ኩፍ ብሎ የነበረው ሲታይ ደግሞ፣ ሥጋ ቁጠር ቢሉት ጣፊያ ያለ፣ ፖለቲካው በሮ ያለቀበት፣ላንባዲና አጥቶ ጨለማ ውስጥ ያለ ድንዝዝ፣ፏንፏ ይላል ዶጁ፣ሽንብራ-ዱቤ-ሽንብራ-ዱቤ እያለ በዋዛ ፈዛዛ እድሜውን የሳለፈ ይመስላል። ኮኮቡ ሲቆጠር ደግሞ፣ፖለቲካ የማይሆነው በኖ የሚጠፋ ከይሲ ነው ይለዋል።

የሲያትል ፎረም ያልገባው በፖለቲካ ዓለም ውስጥ እሳትን በጨርቅ መቃጠር እንደማይቻል ነው። ይልቅስ አዳሜ ጨርቅህ እንዳይቃጠል ከመቋጠር ይልቅ እሳቱን ማጥፋት ይበጃል።

አገር ወዳድ ልብ በል!!

እነዚህ <u>**የሚታዩ**</u> የፖለቲካ ተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ጊዜያዊ፣ መንገድ ላይ የሚቀሩና ጤዘው የሚበኑ ናቸው።

በሌላ በኩል ግን <u>**የማይታየው**</u> ያገር ወዳጹ የፖለቲካ ተቃውሞ እንቅስቃሴ አሸናፊና ዘላቂ ሕዝባዊ ኃይል ነው።

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል !**

**አገር ይድናል !!**

**ምንጊዜም ኢትዮጵያ፣ኢትዮጵያዊነትና ሰንደቅ ዓላማ !!**

12/16/11 (6/4/04)